| | |
|---|---|
| ዐይነት ፤ | ርእስ ፡ አንቀጽ ። |
| ርእስ ፤ | "የሕዝብና ፡ የሀገር ፡ ንብረት ፡ በዐምባ ፡ ገነኖች ፡ ሊሸጥ ፡ ... ።" |
| ደራሲ ፤ | ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፥ ጊዜያዊ ፡ ፈጻሚ ፡ ምክር ፡ ጽ. ፡ ቤት ። |
| ዕለት ፤ | ጥር ፡ 2012 ፡ ዓ.ም. ። |
| ዝግጅት ፤ | ፍጹም ። |
| መጽሔት ፤ | "ሥልጡንሕዝብና" ፡ መዜንው ፥ ቍ.2012-003 |
| ማስታወሻ ፤ | |
| ማሳሰቢያ ፤ | |

እግዚእናችንን ፡ የማስከበር ፥
ሕገ ፡ መንግሥታችንን ፡ የመሥራት ፥
ሥልጡንሕዝባዊ ፡ የርትዕ ፡ መንግሥታችንን ፡ የማቆም ፡
ሀገራዊ ፡ ዐላማችንን ፡ ለመፈጸም ፥ በኢትዮጵያና ፡ በመላው ፡ ዓለም ፡ የምንገኝ ፡ ሀገራውያን ፡ ኢትዮጵያውያን ፥ ሕዝባዊ ፡ አንድነታዊ ፡ አካላችን ፡ ለኾነው ፡ ለኢ.ሀ.ሥ.አ. ፡ እናብር!
ኢ. ሀ ሥ አ
የኢትዮጵያውያን ፡ ሀገራዊ ፡ ሥልጡንሕዝባዊ ፡ አንድነት ።
ሥልጡንሕዝብና ።
www.slttunhzb.net

# ርእስ ፡ አንቀጽ ።

editorial | éditorial | اِفْتِتاحي

## የሕዝብና ፡ የሀገር ፡ ንብረት ፡ በዐምባ ፡ ገነኖች ፡ ሊሸጥ ፡ ... ።

---

የሀገርን ፡ አንጡራ ፡ ሀብት ፡ የመጠበቅ ፣ የመከባከብ ፣ የማልማት ፣ የመሸጥ ፣ የመለወጥ ፡ መብትና ፡ ኀላፊነት ፡ የተገቢ ፡ መንግሥት ፡ ኹሉ ፡ ድርሻ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ይታመናል ።

የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ፡ ዐምባ ፡ ገነን ፡ አገዛዝ ፡ የኢትዮጵያን ፡ መንግሥታውያን ፡ ድርጅቶችን ፡ ለውጭ ፡ ባለሀብቶች ፡ እሸጣለኹ ፡ ብሎ ፡ በዋና ፡ ኀላፊው ፡ በዶክተር ፡ ዐቢይ ፡ አሕመድ ፡ አንደበት ፡ ሲያስታውቅ ፥ በሌለው ፡ ሥልጣን ፡ መወሰኑ ፡ እንደተጠበቀ ፡ ኾኖ ፥ የውሳኔውን ፡ አመክንዮ ፡ ለመረመረው ፥ በኹለቱ ፡ መኻከል ፡ የቀደመ ፡ የተጠቃቃሚነት ፡ ስምምነት ፡ መኖሩን ፡ ያረጋግጣል ።

ዐምባ ፡ ገነን ፥ የውንብድና ፡ አገዛዝ ፡ ዘመኑን ፡ ለማርዘም ፡ ሲጠበብ ፥ ተጨቋኙ ፣ ተበዝባዡ ፡ ሕዝብስ ፡ ምን ፡ ሲሠራ ፡ ቈየ ፦ እያንዳንዱ ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ መልሱን ፡ ይስጥበት ።

ይህ ፡ ነገር ፡ ሰፋ ፡ ያለ ፡ ችግርን ፡ ይጠቊማል ፤ ከኢትዮጵያ ፡ ዐልፎ ፡ በመላ ፡ ዓለም ፡ እግዚእናቸውን ፡ ያላስከበሩ ፡ ሀገሮች ፡ ኹሉ ፥ በዐምባ ፡ ገነኖች ፡ አማካይነት ፥ ንብረቶቻቸው ፡ አንድ ፡ ባንድ ፡ ለምልክዮሽ ፡ ኀይሎች ፡ ሲቸበቸቡባቸው ፡ ይኖራሉ ። የሽያጩ ፡ ገንዘብም ፡ እውጭ ፡ ሀገር ፡ እባንክ ፡ ሒሳብ ፡ ካልገባ ፥ ለጭቈና ፡ ኀይል ፡ ማደርጃና ፡ ለጨቋኞች ፡ ድሎት ፡ ማሟያ ፡ ከመዋል ፡ ሌላ ፡ ለሀገር ፡ ጠብ ፡ የሚል ፡ ነገር ፡ አይኖርም ። ነገሩ ፡ በዚህ ፡ አያበቃም ፤ ነገም ፡ ከነገ ፡ ወዲያም ፡ ምዝበራው ፡ ይቀጥላል ❖


©ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፥ 2012 ፡ ዓ.ም. ።